የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ፍትህ ቢሮ
Central Ethiopia Region State Justice Bureau

ቁጥር 002-25/5266
ቀን 05/05/2017

ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሳይንስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ

ወራቤ

ጉዳዩ፡- <u>የተመዘገበ መመሪያ መላክን ይመለከታል</u>

ከመግቢያው ለመግለጽ እንደተሞከረው ቢሮችሁ በቁጥር ማ/ኢ/ሳ/ኢ/ቴ/ቢ.0078/01/11-113 በቀን 21/04/2017 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ከዚህ ቀደም ሲጠቀምበት የነበረውን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ፣አገልግሎት እና መሰረተ ልማት አቅርቦት መመሪያን እንዲመዘገብልን በማለት መጠየቃችሁ ይታወቃል፡፡

በዚህ መሰረት ከተቋማችሁ የመጣውን መመሪያ በጥልቀት ፈትሸን በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የአስተዳደር ሥነ ስርአት አዋጅ ቁጥር 23/2016 አንቀጽ 16/2/ መሰረት በዛሬው ቀን ማለትም ጥር 5/2017 ዓ/ም " **የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ሳይንስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ያወጣውን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ፣አገልግሎት እና መሰረተ ልማት አቅርቦት መመሪያ ቁጥር 05/2017 ዓ.ም** "ሆኖ የተመዘገበ መሆኑን እየገለጽን በክልሉ የአስተዳደር ሥነስርአት አዋጅ ቁጥር 23/2016 አንቀጽ 17/4/ መሰረት ተቋማችሁ መመሪያውን ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል ለተጠቃሚዎች በመመሪያው ይዘት ላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እንዲሰራ ፣መሪያው ስካን ተደርጎ በፒዲኤፍ ፎርማት በቢሯችሁ ድረ ገጽ ላይ እንዲጫን እንዲሁም መመሪያውን በማሳተም ለሚመለከታቸው መንግስታዊ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲሰራጭ ወይም ማንኛውም የመመሪያ ቅጅ ማግኘት ለሚፈልግ ሰው መመሪያውን ባለበት ሁኔታ የመመልከት ወይም ወጪውን ሸፍኖ ከቢሯችሁ እንዲያገኝ እንዲደረግ እያሳሰብን <u>09</u> ገጽ የያዘውን መመሪያ በዚህ ደብዳቤ ሸኝነት የላክን መሆናችንን እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

አህመዲን ሶማ
Ahmedin Soma
የፍትህ ቢሮ ኃላፊ
Head of Justice Bureau

<u>ግልባጭ</u>

- ለቢሮ ኃላፊ ጽ/ቤት
- ለህግ ጉዳዮች ዘርፍ
- ለህግ ጥ/ማ/ማ/ ዳይሬክቶሬት<u>**ፍትህ ቢሮ**</u>

ፖ/ሳ.ቁ የመ.ሣ.ቁ 291
P.O. Box
ስ.ቁ 046 220 58 00
Tel
ፋክስ 046 221 24 37
Fax
emal:- justicebureauplan@gmail.com

ፍትህ ለሁሉም!!!Justice for All!!!

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ
Central Ethiopia *Regional State Science & Information Technology Bureau*

ቁጥር ማኢ/ሳኢ/ቴቢ/
ቀን 21/02/2017 ዓ.ም

ለማዕ/ኢት/ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ

ሆሳዕና

ጉዳዩ፡- መመሪያ እንዲመዘገብልን ስለመላክ ይሆናል፣

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው ማዕከላዊ ኢትዮጲያ ክልል ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ለስራ መተግበሪያ የሚሆን መመሪያ ማለትም "የኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶችና መሰረተ ልማት አቅርቦት አፈጻጸም መመሪያ" በቀድሞ ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት የነበረዉን ወደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ቀይረን /አሻሽለን/ አዘጋጅተን ከቢሯችሁ የተሰጡትን አስተያየቶች አካተን በመኔጅመንት አጽድቀን የላክን መሆኑን እየገለጽን የማኔጅመንት ዉይይት ቃለ-ጉባኤ ከዚህ ሽኝ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን ጭምር እየገለጽን መመሪያዉ እንዲመዘገብልን እንጠይቃለን፡፡

/// ከሰላምታ ጋር ///

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ
- ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ስርጸት ዘርፍ
- ለኢኮቴ ልማትና አስተዳደር ዘርፍ
- ለቢሮ ኃላፊ አማካሪ

ሳኢ.ቴቢ፣

Tele:- 046-771-08-49
- 046-771-07-92
- 046-771-49-63
Facebook : - www.facebook.com /Science and Information Technology Bureau
Website:-www.sictcb.gov.et Email : - scsiproha02@gmail.com https://10.208.215.9/owa
Telegram:-*Science and Information Technology Bureau*

# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

## ማዕከላዊ ነጋሪት ጋዜጣ

## MAEKELAWI NEGARIT GAZETA

## OF THE CENTERAL ETHIOPIA REGIONAL STATE

ወራቤ 2ኛ ዓመት ቁጥር ታህሳስ 10 ቀን ዓ.ም 2017

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Worabe 2nd Year No December /2024

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሳይንስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ

# "የኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች እና መሰረተልማት አቅርቦት አፈጻጸም መመሪያ" ቁጥር 05/2017

## መግቢያ

በዓለማችን በማደግ ላይ ለሚገኙ ሀገራት የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ለልማትና ለዕድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑ እሙን ነው፡፡ ሀገራችንም በቅርቡ የመካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ የምታደርገው ጥረት በሀገር ደረጃ የሳይንስና ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ወጥቶለት ትግበራ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በዘርፉ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

በክልላችንም ሀገራዊ የልማት አቅጣጫን በተከተለ ሁኔታ በየደረጃው የሚገኙ የመንግስት ተቋማትንና ህብረተሰቡን የኢኮቴ ተጠቃሚ ለማድረግ የተከናወኑ ተግባራት በቂ ናቸው ባይባልም ቀላል ግምት የሚሳጣቸው አይደሉም፡፡ በቀጣይ ከክልል እስከ ወረዳና ከተማ የአስተዳደር እርካኖች ድረስ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራትን በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ በማስደገፍ በውጤታማነት ለመፈጸም የኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች እና መሠረተ-ልማት አቅርቦት ስርዓት ባለው በውጤታማነት እና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ መምራትና ለመፈጸም የሚያስችል መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በመሆኑም የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ለማቋቋም ባወጣው አዋጅ 199/2015 አንቀጽ 39 (2) በተሰጠው ሥልጣንና ተግባራት መሠረት የኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች እና መሠረተ-ልማቶች አቅርቦትን በተሻለ ሁኔታ ለመምራት እና ለመደገፍ እንዲያስችለን የተለያዩ የባለድርሻ አካላት ሚና በመለየት ይህ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ የኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች እና መሰረተ ልማት አቅርቦት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 001/2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፦

1. **"ክልል"** ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ነው፡፡
2. **"ቢሮ "** ማለት የክልሉ ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ነው፡፡
3. **"የመንግስት መስሪያ ቤት"** ማለት በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የተቋቋመ የክልል ሴክተር መስሪያ ቤት ሆኖ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር መስሪያ ቤት፣ ተቋም ወይም አካል ሲሆን በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ መንግስታዊ ተቋማትና የልማት ድርጅቶችንም ይጨምራል፡፡
4. **"የበላይ ኃላፊ"** ማለት የመንግስት መሥሪያ ቤቶችን በዋና ኃላፊነት ተመድቦ የሚመራ ሰው ነው፡፡
5. **"ኢኮቴ"** ማለት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ነው፡፡
6. **"ሳኢቴ"** ማለት ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ነው፡፡
7. **"ስፔሲፊኬሽን"** ማለት የኢኮቴ መሳሪያዎችና አገልሎቶች ዝርዝር መግለጫ ነው፡፡
8. **"መሰረተ ልማት"** ማለት ለመረጃ ልውውጥ አገልግሎት የሚውሉ የመረጃ መረብ አውታር እና ሲስተም ትስስር ነው፡፡
9. **"አቅራቢ"** ማለት ለግዢ ፈጻሚ አካላት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ዉል የገባ ግለሰብ ወይም ድርጀት ነው፡፡
10. **"ቴክኒካል ሰነድ ግምገማ"** ማለት ስፔስፊኬሽን ሰነድ ላይ የተመላከቱ ዝርዝር መግለጫ እና ሌሎች የግምገማ መስፈርቶችን የያዘ ሰነድ የማመሳከሪያ ሂደት ነው፡፡
11. **"የሲስተም ልማት ዑደት"** ማለት ከፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ጀምሮ እስከ ትግበራ ምዕራፍ ድረስ የሚተገበር የሲስተም ልማት ሂደት ነው፡፡
12. **"ሲስተም ሪኳየርመንት"** ማለት ለሲስተም ልማት ዝርዝር ቅድመ ሁኔታና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ሰነድ ነው፡፡
13. **"የኢኮቴ መዋቅሮች"** ማለት የክልሉ ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮን ጨምሮ በክልል ተቋማት የተደራጁ የኢኮቴ ዳይሬክቶሬቶች/[illegible] የስራ ሂደት፣ በዞን፣በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ፣

በከተማ አስተዳደር የተደራጁ ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መምሪያ፣ ጽ/ቤት፣ ዩኒት ነው፡፡

14. "**የአስተዳደር እርከኖች**" ማለት ክልል፣ ዞን፣ ልዩ ወረዳ፣ ወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

**3. ዓላማ**

በኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች እና መሰረተ ልማት ግዢ ስርዓት በክልሉ ውስጥ ሁሉም የመንግስት ተቋማት የሚኖራቸውን ሚናና ኃላፊነት በግልጽ በማስቀመጥ የግዢ ስርዓት ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

**4. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በክልሉ ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ ሁሉም ዞኖች፣ ልዩ ወረዳዎች፣ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች እና መሰረተልማት ተጠቃሚዎች በሙሉ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**5. የመመሪያው አስፈላጊነት**

ይህ መመሪያ በየደረጃው የሚገኙ የመንግስት ተቋማት የኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች እና መሰረተ ልማት አቅርቦትን ለማዘመን መመሪያው የሚከተሉት ዝርዝር ፋይዳዎች ይኖሩታል፡-

1. የመንግስትን በጀት በአግባቡ በመጠቀም የኢኮቴ መሳሪያዎችን፣ አገልግሎቶች ግዢ እና የመሰረተ ልማት ግንባታ አላስፈላጊ ድግግሞሽ በማስቀረት የሀብት ብክነትን ለመቀነስ፤
2. የኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች እና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ስራ በሚመለከተው አካል በማሰራት ወቅታዊ ጥራቱን የጠበቀ፣ ከኪራይ ሰብሳቢነት የጸዳ ግዢ ለማከናወን እና ግልጽ የአቅርቦት አሰራር ስርዓት ለማስፈን፤
3. የኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች እና የመሰረተ ልማት ስፔስፊኬሽን ዝግጅትና ግምገማ ስርዓት ወጥነት ባለው ሁኔታ የአሰራር ሂደቶችን ተከትሎ ለመተግበርና አፈጻጸም ለመቆጣጠር እንዲቻል፤
4. የኢኮቴ መሳሪያዎችን፣ አገልግሎቶች እና የመሰረተ ልማቶች ደረጃቸውን የጠበቀ፣ ዉጤታማ እና ተገቢውን ግዢ ለመፈጸም እንዲቻል፤
5. በኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች እና መሰረተ ልማት አቅርቦት ዙሪያ የባለድርሻ አካላትን ሚና በመለየት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማድረግ፤

## ክፍል ሁለት

## ተግባርና ኃላፊነትን ስለማሳወቅ

### 6. የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

1. የኢኮቴ መሳሪያዎች፤ አገልግሎቶች እና የመሰረተ ልማት ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ያሻሽላል፤
2. ለመመሪያው አተገባበር አጋዥ የሚሆኑ የአሰራር ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፤
3. በክልል ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሚቀርቡ የኢኮቴ መሣሪያዎች አቅርቦት ዙሪያ ቴክኒካል ድጋፍ ጥያቄዎች መሠረት ወቅታዊ ድጋፍ ያደርጋል፤
4. ለክልሉ ተቋማት በኢኮቴ ፕሮጀክቶች ዝግጅት ግምገማና ትግበራ ዙሪያ የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤
5. በየደረጃው ለሚገኙ የኢኮቴ መዋቅሮች የተሰጠ ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊነቱ ሲታመንበት በፕሮጀክት አተገባበር ሂደት ድጋፍ በተጠየቀ ጊዜ ለሚመለከተው የበላይ አካል በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤
6. የመመሪያውን ተፈጻሚነትን ይከታተላል፤ ጥሰት ተፈጽሞ ሲገኝ ለሚመለከታቸው አካላት በማቅረብ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
7. በዘርፉ የመንግስት ግዥ አፈጻጸም ሂደት በሚቀርቡ የቴክኒክ ጉዳዮች፣ ቅሬታዎችና ጥያቄዎች ላይ ቴክኒካል ማብራሪያ ወይም አስተያየት እንዲሰጥ ጥያቄ ሲቀርብ ለሚመለከተው አካል ምላሽ ይሰጣል።

### 7. የፋይናንስ ሴክተር ተግባርና ኃላፊነት

1. የመንግስት ተቋማት የኢኮቴ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች እና የመሰረተ ልማት ግዢ የበጀት ጥያቄ ሲቀርብ ቢሮው እና በየደረጃው በሚገኙ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መዋቅሮች በተሰጣቸው ኃላፊነት ልክ ተገምግሞ አዎንታዊ አስተያየት የተሰጠበት ስለመሆኑ ያረጋግጣል፤
2. ይህንን መመሪያ ከመደበኛው የመንግስት ግዢ ህግ ማዕቀፍ ጋር ተጣጥሞ እንዲፈጸም ያደርጋል።

### 8. የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

1. የኢኮቴ መሳሪያዎችን፣ አገልግሎቶች እና የመሰረተ ልማት ግዢ ፍላጎት አዘጋጅተው ለየመዋቅራቸው ፋይናንስ ሴክተር ያቀርባሉ፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል መዋቅር ቢሮዎች ስር የኢኮቴ ዳይሬክቶሬቶች የኢኮቴ መሳሪያዎችን፣ አገልግሎቶች እና የመሰረተ ልማት ግገር ፍላጎት ተጠሪ ለሆኑለት ቢሮ ያሳውቃሉ፣
3. ባቀረቡት የግገር ፍላጎት መሠረት አገልግሎቱ እስኪቀርብላቸው ድረስ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፣

## 9. የዞን/ልዩ ወረዳ እና ወረዳ/ከተማ አስተዳደር ሳኢቴ ሴክተር ተግባርና ኃላፊነት

1. ለየመዋቅሮቻቸው ፋይናንስ መስሪያ ቤቶች የቀረቡ የኢኮቴ መሣሪያዎች ፍላጎት ሟሟላት የሚያስችሉ ወቅታዊ ስፔሲፊኬሽን ሰነዶችን አዘጋጅተው ለፋይናንስ መዋቅሮቻቸው ያቀርባሉ፣
2. በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት ለየመዋቅሮቻቸው የስፔሲፊኬሽን ሰነድ እንዲሁም ከአቅራቢ ድርጅቶች የሚቀርቡ መሣሪዎችን ቴክኒካል ግምገማ ያደርጋሉ፤ ወቅታዊ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ያቀርባሉ፣
3. ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የቴክኒክ ሥራዎችን ያከናውናሉ።

## ክፍል ሶስት

## የቴክኒካል ሰነድ ዝግጅት፣ ግምገማና ትግበራ

**10. የኢኮቴ መሳሪያዎች አቅርቦት ሂደት**

1. ማንኛውም የኢኮቴ መሳሪያዎች የግዢ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት የፍላጎት መግለጫ መቅረብ አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበውን የፍላጎት መግለጫ መነሻ በማድረግ ስፔስፊኬሽን ይዘጋጃል፤ የግዢ ጨረታ ሰነዱም በዚሁ ስፔሲፊኬሽን መሠረት ይዘጋጃል፤
3. የተጫራቾች ሰነድ ምርመራ በግዢ ጨረታው ከተያያዘው ስፔሲፊኬሽን አንጻር ይገመገማል፤
4. በአሸናፊ ድርጅት የሚቀርቡ ዕቃዎች በተዘጋጀው ስፔስፊኬሽን ሰነድ መሰረት እየተገመገመ እርክክብ የሚፈጸም ይሆናል፤

**11. የኢኮቴ መሳሪያዎች ስፔሲፊኬሽን ዝግጅት ሂደት**

1. የኢኮቴ መሳሪያዎች ስፔሲፊኬሽን ሰነድ ዝግጅት የሚከናወነው ዕቃው ያስፈለገበትን ዓላማ መሠረት አድርጎ ነው። በመሆኑም ግዢ እንዲፈጸምለት የሚፈልግ አካል ለቢሮው ወይም ለመምሪያዎች ወይም ለጽ/ቤቶች በሚያቀርበው ደብዳቤ መሳሪያው የተፈለገበትን ዓላማ በግልጽ ማስፈር አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበው የፍላጎት ማሳወቂያ ደብዳቤ መሠረት ስፔሲፊኬሽን ሰነዱ ተዘጋጅቶ፤ በሚመለከተው የዘርፍ ኃላፊ ወይም ዳይሬክተር ወይም ቡድን መሪ ሲጸድቅ ተፈጻሚ ይደረጋል፤
3. በኢኮቴ መሳሪያዎች ስፔስፍኬሽን ዝግጅት እና ግምገማ ወቅት ቢያንስ ሁለት የኢኮቴ ባለሙያዎች መሳተፍ ይኖርባቸዋል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሙያ እጥረት የሚገጥማቸው መዋቅሮች በአስተዳደር እርከናቸው ወይም አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ከሚገኘው መዋቅር የባለሙያ ትብብር በመጠየቅ ወይም የተዘጋጀ ስፔስፊኬሽን ሰነድ በማግኘት ማከናወን ይችላሉ፤
5. በዚህ ሒደት የሚያጋጥሙ ችግሮች ሲኖሩ ከቢሮው ጋር በመናበብ ወቅታዊ ምላሽ እንዲያገኙ በማድረግ በሚቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋል።

**13. የኢኮቴ መሳሪያዎች የቴኒካል ሰነድ ግምገማ ሂደት**

1. የኢኮቴ መሳሪያዎች ቴክኒካል ሰነድ ግምገማ ጥያቄ ሲቀርብ የግምገማው ስርዓቱ የተሟላና ትክክለኛ ሰነድ መቅረቡን በማረጋገጥ ይጀመራል፤

2. በኢኮቴ መሳሪያዎች የቴክኒካል ሰነድ ግምገማ ወቅት ቢያንስ ሁለት የኢኮቴ ባለሙያዎች መሳተፍ አለባቸው፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2. የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሰው ኃይል እጥረት የሚገጥማቸው ተቋማት ቢሮውን በመጠየቅ የባለሙያ ድጋፍ ጠይቀው ማከናወን ይችላሉ፤

4. የኢኮቴ መሳሪያዎች ስፔስፊኬሽን ዝግጅት ወቅት የተሳተፈ ባለሙያ በሰነድ ግምገማ ወቅት መሳተፍ አይችልም፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሙያ እጥረት የሚገጥማቸው መዋቅሮች በአስተዳደር እርከናቸው ወይም አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ከሚገኘው መዋቅር የባለሙያ ትብብር በመጠየቅ ግምገማውን ማከናወን ይችላሉ።

## 14. በአሸናፊ አቅራቢ ድርጅት የቀረበ የኢኮቴ መሳሪያዎች ግምገማ ሂደት

1. አሸናፊ ተጫራቾች የሚያቀርቧቸው የኢኮቴ መሳሪያዎች ቴክኒካል ግምገማ የተሟላና ትክክለኛ ሰነድ መቅረቡን በማረጋገጥ ይጀመራል፤

2. የቀረቡ መሳሪያዎች ትክክለኛነት በጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዞ በወጣው ስፔሲፊኬሽን መሠረት ብቻ እየተገመገመ ይረጋገጣል፤

3. በተዘጋጀ ስፔስፊኬሽን መሠረት በሚካሔድ የኢኮቴ መሳሪያዎች ግምገማ ወቅት የቴክኒካል ግምገማ ላይ የተሳተፉ ባለሙያዎችን ጨምሮ ቢያንስ ሁለት የኢኮቴ ባለሙያዎች መሳተፍ አለባቸው፤

4. የኢኮቴ መሳሪያዎች የቴክኒካል ሰነድ ግምገማ ውጤት በየደረጃው ለሚገኙ የፋይናንስ መዋቅር በደብዳቤ ይገለጻል።

## 15. የኢኮቴ አገልግሎቶች ቴክኒካል ሰነድ ወይም ሪኳየርሜንት አናሊሲስ ሰነድ ዝግጅት

1. ማንኛውም የኢኮቴ አገልግሎቶች ቴክኒካል ወይም ሪኳየርሜንት አናሊሲስ ሰነድ ዝግጅት ጥያቄ አገልግሎቱ ያስፈለገበትን ዓላማ የሚገልጽ ደብዳቤ በየደረጃው ለሚገኙ የሳኢቴ መዋቅር መቅረብ አለበት፤

2. ከተቋማት በቀረበው ጥያቄ መሰረት የኢኮቴ አገልግሎቶች ቴክኒካል ሰነድ ወይም ሪኳየርመንት አናሊሲስ ሰነድ በየደረጃው በሚገኙ የሳኢቴ መዋቅር ተዘጋጅቶ በሚመለከተው ኃላፊ ሲጸድቅ ጥቅም ላይ ይውላል፤

## 16. የኢኮቴ አገልግሎቶች ቴክኒካል ሰነድ ወይም ሪኳየርሜንት አናሊሲስ ሰነድ ግምገማ ሂደት

1. የኢኮቴ አገልግሎቶች ቴክኒካል ሰነድ ወይም ሪኳየርሜንት አናሊሲስ ሰነድ ግምገማ ሂደት የተሟላና ትክክለኛ ሰነድ መቅረቡን በማረጋገጥ ይጀመራል፤

2. በኢኮቴ አገልግሎቶች የቴክኒካል ሰነድ ግምገማ ወቅት ቢያንስ ሁለት የኢኮቴ ባለሙያዎች መሳተፍ አለባቸው፤

3. የኢኮቴ አገልግሎቶች ቴክኒካል ወይም ሪኳየርሜንት አናሊሲስ ሰነድ ዝግጅት ወቅት የተሳተፈ ባለሙያ በሰነድ ግምገማ ወቅት መሳተፍ አይችልም፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሙያ እጥረት የሚገጥማቸው መዋቅሮች በአስተዳደር እርከናቸው ወይም አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ከሚገኘው መዋቅር የባለሙያ ትብብር በመጠየቅ ግምገማውን ማከናወን ይችላሉ፡፡

## 17. በአሽናፊ አቅራቢ ድርጅት የቀረበ የኢኮቴ አገልግሎቶች ወይም ሲስተም ልማት ግምገማ ሒደት

1. አሸናፊ ተጫራቾች የሚያቀርቧቸው የኢኮቴ አገልግሎቶች ቴክኒካል ግምገማ የተሟላና ትክክለኛ ሰነድ መቅረቡን በማረጋገጥ ይጀመራል፤

2. በአሸናፊ አቅራቢ ድርጅት የቀረቡ የኢኮቴ አገልግሎቶች እያንዳንዳቸው በጥንቃቄ ለጨረታው በወቅቱ በቀረበው ቴክኒካል ወይም ሪኳየርሜንት አናሊሲስ ሰነድ መሰረት ብቻ መገምገም ይኖርበታል፤

3. በኢኮቴ አገልግሎቶች ግምገማ ወቅት የቴክኒካል ሰነድ ግምገማ ላይ የተሳተፉ ባለሙያዎችን ጨምሮ ቢያንስ ሁለት ባለሙያዎች መሳተፍ አለባቸው፤

4. በሲስተም ልማት ሂደት በጥናት ሰነድ መሰረት ከዲዛይን ጀምሮ እስከ ትግበራ ምዕራፍ ድረስ የሚኖሩትን የሲስተም ልማት ዑደትን ተከትሎ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፤

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ
Central Ethiopia Regional State Science & Information Technology Bureau

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. መመሪያውን ስለማሻሻል

1. ይህንን መመሪያ ቢሮው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሊያሻሽለው ወይም ሊለውጠው ይችላል።
2. በዚህ አንቀፅ የንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው መመሪያው በተሻሻለ በማናቸውም ጊዜ ለፍትህ ቢሮ መመሪያው የተሻሻለ ስለመሆኑ በማሳወቅ ማስመዘገብና ቁጥር እንዲሰጥ ማድረግ አለበት።

### 19. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ እና የዚህን መመሪያ መሰረት አድርገው የሚወጡ የአፈጻጸም ማንዋሎችን የመተባበር ግዴታ አለበት።

### 20. ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች

ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የለውም።

### 21. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሳይንስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ማኔጅመንት ጸድቆ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ከተመዘገበበት ከጥር 5 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አቶ ሳለሙ አማዶ

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ኃላፊ